## ሓወልቶች አወሩ

ከውጭ ሃገር ሄዶ ዓለሙን ጐብኝቶ
ብዙ ዓንጀባና ክብርም ተቀዳጅቶ
በናፍቆት ሲስሙት፣ ሲደባብሱት
ባንዴራም ደርበው አለባብሰውት
በዘፈን፣ በደስታ፣ ድምፀ መለከት
አገሩ ሲገባ እንግዳው ሓወልት
ታላቅ አቀባበል አድርገውለት
በቅናት፣ በቁጭት ነባሩ አይቶት፤



“ምን ታደርግ መጣህ ወደ ድኽነት
ከዚያ አይሻልም ወይ ከነበርክበት
ደህና ለባብሰሃል፣ የተራብክ አትመስልም
ከኋላ ቀርነት ስልጣኔ አይሻልም!
ካገር እወጣለሁ እያልኩ ስመኝ እኔ
ምን ታደርግ መጣህ ከዚህ ከኩነኔ?
ተጣምሜያሁኝ፣ ልወድቅ ያሰጋኛል
አሁን ያንተ መምጣት መቸ ይገባኛል!
ታላቅ ወንድማችን ያውልህ ከጐኔ
ወድቆ ተሰባብሯል፣ ወይኔ! ወይኔ!
እስቲ አጫውተኝ ስለ ስልጣኔ
ስለ ብልጽግና፣ ስለ ሃብት ምጣኔ...”



ብሎ ቢጠይቀው እያለቃቀሰ
በዕንባ ዓይኖቹን ደጋግሞ እያራሰ
ስደተኛው ሓወልት እንዲህ ሲል መለሰ፤
“ስደት፣ መንገላታት ከብዙ መከራ
ውጣ፣ ውረድ አለው፣ ስንቱን ብየ ላውራ
በትሬንታ ኳትሮ፣ ደግሞም በመርከብ፣
ከዚያም ባውሮፕላን፣ ያውም አንቶኖቭ፣
ከአንዱ ወደ ሌላው ሲያንከራትቱኝ፣
ከመሬት፣ ከባሕር፣ ከአየር ሲያወጡኝ፣
እናስተምር ብለው ሊያሰለጥኑኝ
ሲቆርጡ፣ ሲፈልጡ፣ ሲጠጋግኑኝ፣
እንዳልሞት፣ እንዳልሽር ጉድ አደረጉኝ!

“ከባዕዱ አገር ሸለቆ፣ ተራራ
እህት፣ ወንድም የለኝ፣ ማንን ብየ ልጥራ

በዕንቅርት ጆሮ ደግፍ አወይ የግዚሃር ሥራ
የተቆራረጥኹት አልበቃኝ መሰለው
መብረቁን ላከና አናቴን በተነው!
እንዲህ ለባብሼ ብመስልህም ደህና
ነፍሴ አትውጣ እንጂ፣ መቼ ሆንኩኝ ጤና?
ተቆራርጫለሁ፣ ተጐሳቁያለሁ፣
ስንቱን አሳልፌ ይኸው መጥቻለሁ።
“እስቲ ተቀበለኝ ‘ወንድሜ!’ ብለህ
ሩቅ ዞሬ ያየሁት ሁሉን ልንገርህ
እኔ አልኮራብህም ቃሌን ልግባልህ
ከተማረኩት ሁሉ ትንሽ ላካፍልህ
በሽሚዜ አትቅና በደረብኩት ልብስ
የቁስሌ ሽፋን ነው፣ እግዚኦ አታድርስ!
ሌት ተቀን ተሠርቶ እፎይታም የሌለው
ስልጣኔ የሚሉት ጉምና ሕልም ነው።
ጠግቦ፣ ተንደላቅቆ ስደት ከመኖር
መጠኑን ለክቶ በልቶ በማደር
በችግርም ቢሆን ከገዛ ሃገር
የሚበልጥ የለም ከነፃነት ክብር!



“በርትተው ከሠሩ ድኽነት ያበቃል
ትንሽ ከታገሱ ችግርም ይለቅቃል
ነባርና እንግዳው አይዞህ ተባብለን
የተጣመመውን ይዘን፣ አቅንተን
የወደቀውንም ወንድማችንን
በርትተን እናንሳው አንድ! ሁለት! ብለን
እንግዲያውስ ስማኝ በሕብረት ሠርተን
ዘር፣ ጐሳ ሳንለይ ተከባብረን
እናልማ ጠንክረን ሃገራችንን።
“ወደፊት ከመግፋት ኋላ ሊያስቀሩን
ለያይተው፣ አጣልተው፤ ‘ደንቆሮ!’ ሊሉን
ከሩቅም፣ ከቅርብም ጠላቶች አሉን።”

ገ/ኢ. ጐርፉ።